## “እናት አገሩን ቆራርሶ ለባዕድ የሰጠ ወይም የሸጠ እና የእናቱን ጡትና እጅ የቆረጠ አንድ ነው” (ቆስታ ዲሞትሮስ)

የሁሉም አገር ዜጎች ተወልዶ ያደጉበትን አገር ይወዳሉ፣ በዚያ አገር ይኮራሉ፣ የዚያን አገር ህልውናና ዳርድንበር ለማስጠበቅ ሕይወታቸውን ይሰጣሉ ። ከትውልድ ወደ ትውልድ የተላለፈ፣ በቅማቅም አያቶች እና አያቶች መሰዋዕትነት የቆየ ቅርስ ፤ የእኔነት ምንጭ ፣ የአንድን አገር ዜጎች ግኝት መሃፀን- በቀማኞችና በግፈኞች ሲነጠቅ ፤ እንደ ሸቀጥ ሲሸጥ ሲለወጥ ማየት የሚፈጥረው የሃዘን ስሜትና ህመም ለመረዳት ወይም ለማወቅ ካስፈለገ ፤

በቅኝ የተገዙትን -አፍሪካውያን ፣ ኤሲያውያን ፣ ደቡብ አሜሪካውያን ፣ ካሬቢያውያን ፣ ፍልስጤማውያን ፣ ለባርነት የተሸጡትን አፍሪካአውያን ፣ ቁያቸውና  መሬታቸው ተነጥቀው ለባእዳን ከበርቴዎች የተሸጠባቸውን ጋቤላውያን ፣ በኦሞ ወንዝ ዙሪያ የሚኖሩትን ሱሪያውያን ፣ መሬታቸው ለሱዳን መንግሥት የተሰጠባቸውን የቤገምድር አርሶ አደሮች ፣ ሃብትና ንብረታቸውን ተዘርፈውና ተቀምተው ከጉራ ፈርዳና ከቤኒሻንጉል የተፈናቀሉትን አማርዎች  ወዘተርፈ መጠየቅ ወይም እነርሱ መሆን ያስፍልጋል ።

‘ቆስታ ዲሞትሮስ’ የተባለ የጥንታዊ ግሪክ ዜጋ ስለእናት አገሩን ያልውን ፍቅርና ዋጋ ሲገልጽ - “እናት አገር ቆራርሶ ለባዕድ የሰጠ ወይም የሸጠ እና የእናቱን ጡትና እጅ የቆረጠ አንድ ነው ” አለ ፤ ያለበት ምክንያትም እንደሚከተልው አብራርቶታል።

- ልጆች ከእናታቸው ፣ እናት ከልጆቿ በደም ፣ በሥጋና በመንፍስ ፍጹም የሆነ ቁርኝት (bondage) አላቸው ፤ በሰዎች መካከል ከዚያ የቀረበ የዝምድና ትሥሥር የለም ። ከማሃጸኗ አንስቶ እስከ ተወልደው አቅመ - ምግብ እስኪደርሱ የጠቡትን ጡቶቿ እና ባላት የማህበርዊ ኑሮ ደረጃዋ በምታገኘው የገቢ ምንጭ - ሸምታ ፣ አብስላ ፣ አብልታ ፣ አጠጥታ ፣ ሲርባቸው ተርባ ፣ ሲጠማቸው ተጠምታ ፣ ሲታመሙ ታማ ፣ ተጨንቃና ተንከባክባ ያሳደገቻቸውን ልጆቿ ‘የጠቡትን ጡቶቹዋና ሥርታ ያበላችበትን እጅዎችዋን’ ቢቆርጡ የሚሰጠው ወይም የሚኖረው ትርጉም  የእብደት ወይም የፍጹም እብደት ድርጊት ነው የሚሆነው ።
- አንድ ጤናማ አእምሮ ያለው ዜጋ - ተወልዶ ካደገበት አገርና ሕዝብ ጋር የሚኖረው ፍቅርና ትሥሥር ከወላጅ እናቱ ጋር ከሚኖረው ፍቅርና የዝምድና ቁርኝት ቢበልጥ እንጂ አያንስም ። ምክንያቱም እናት አገር የአንድን አገር ዜጎዎች ሁሉ መፈጠርያና መቀበርያ ማሕፀን ናት ። እናት ሟች ናት ፣ እናት አገር ግን ዘላለምዓዊት ናት ፤ እናት አገር ከማህፀኗ በሚወጡ - ወንዞች ፣ ምንጮች ፣ ኩሬዎች ፣ ሃይቆች ፣ እህሎች ፣ አትክልቶች ፣ ፍራፍሬዎች ፤ ከአዝእልቷ በሚወጡ የአየር ዓይነቶች ፣ ከአናቷ ላይ በሚዘንቡ ወቅታዊ ዘናብዎቿ፣ ከአናቷ ላይ ከምታገኘው የፀሐይ ሙቀት - ባጠቃላይ ተፈጥሮ በለገሳትን ሃብቷና መንፈስዋ ወይም አድባርዋ- ከአብራኳ የወጣነውን ልጆቿን ፣ አእዋፍቶቿን ፣አራዊቶቿን ፣ ባጠቃላይ ነፍስ ያላቸው ፍጥረቶቿን በሙሉ - መግባ ፣ አጠጥታ ፣ ኮትኩታና ሕይወት ሰጥታ ታኖረናለች ።
- በመሆኑም ‘በሥልጣን ተምክተውም ሆነ በአፍቅሮተ ነዋይ ተሰልበው’ - ተወልደው ያደጉበትና - የዘር ዝሪያቸውን እትብትና አጽም የተሸከመችውን እናት አገራችውን ቆራርሶ ለባዕዳን የሚሰጡ ወይም የሚሸጡ - “የእናቶቻቸውን ጡትና እጅ እንድ ቆረጡ ይቆጠራል ወይም ይመስላሉ”

በማለት ትምህርት ሰጥቶ አልፍዋል (ቆስታ ዲሞትሮስ) ። ከዚህ ጠለቅ ካለ ፍልስፍናዊ አመለካከት ወይም ግንዛቤ አንጻር - ወያኔዎች በእናት አገራችን ላይ የፈጸሙትና በመፈጸም ላይ ያሉትን ደባ **የእናቶቻቸውን ጡትና እጅ የቆረጡ ያሰኛቸዋል ማለት ነው** ።

- ቆስታ ዲሞትሮስ እናት አገርን አስመልክቶ ለምን የዚህ ዓይነት ሥነልቦና የሚነካ አጽናዎት (emphasis) እንዳደረጉ ባይገለጽም በ 'ኤክሌሲያ (Ecclesia)' ካደረጉትን ንግግራቸው የተወሰደ ወይም የተጨለፈ ነው ። ኤክሌሲያ (Ecclesia) ብሔራዊ ምላዓተ ጉባኤ ወይም ሸንጎ (the national popular assembly) ማለት ነው ።
- በአምስተኛው ም.ዓለም (5 BC) የአቅመ አዳም ያልደረሱትን፣ ባሬያዎችና ሴቶችን ሳይጨመሩ በአቴንስ ከተማና ዙርያዋ ይኖሩ የነበሩትን የግሪክ ዜጎች የአገራቸውን - ፖለቲካዊ ፣ ማህበራዊ ፣ አስተዳደራዊ ፣ ወታደራዊ ፣ ፍትሃዊ ፣ ሕገመንግሥታዊ ፣ እምነታዊ ወዘተርፈ ጉዳዮቻቸው ላይ በቀጥታ የሚሳተፉበት ፣ የሚወያዩበት ፣ የሚደስኩሩበት ፣ የሚከራከሩበት ፣ የሚሟገቱበት - የአደባባይ ብሔራዊ ምላዓተ ሸንጎ (Ecclesia) ነበራቸው ። ኤክሌሲያ የተወካዮች ሸንጎ ወይም ምክር ቤት (house of representatives parliament) ሣይሆን - የቀጥታ ዲሞክራሲያዊ ሥራዓት ናሙና (direct democratic system model) ነበር ። 'እክሌሲያ' አሁን እስከ አለንበት 21ኛ መቶ ክፍለ ዘመን ዲሞክራሲ ! ዲሞክራሲ ! እያልን ለምንጮህለት የመልካም አስተዳደር ሥራዓት - የመሠረት ድንጋይ የጣለ ነው ።
- ለምን ይሆን ቆስታ ዲሞትሮስ የዚያን ዓይነት ንግግር ለማድረግ የተገደዱት? በዚያን ታሪካዊ ወቅት ግርክ በበርካታ ትናንሽ ግዛቶች ተከፋፍላ ስለነበረ ፤ ለዚያ መከፋፈል የወቅቱ ገዢዎች አስተዋጽኦ አድርጎዋል ማለታቸው ይሆን? አንዱን ገዢ ለሌው ገዢ መሬት ቆርሶ ሲሸጥ ሲለወጥ ዓይተው ይሆን ? ወይስ በ21ኛ መቶ ክፍለ ዘመን በኢትዮጵያ በዚያኔ ግሪኮዎች አጠራር ግን (ኤትዮጵያ) - ጥቁር ወይም ፀሓይ ቃጠል ቀለም ያለው ሕዝብ አገር ላይ እንደ ሚከስት ታይቷቸው ይሆን ? እስቲ ቆስታ ዲሞትሮስ ስለእናት አገር የነበራቸውን ጥልቅ ግንዛቤና ፍልስፍናዊ ትምህርት እዚህ ጋ ልቋጭና የእኔ የበኩሌን ላክልበት ።

እናት አገር ማስነጠቅ እናትን ከመግደል የከፋ ክህደት ነው እላለሁ ። ከሱዳን ድንበር ፣ ከጉራ ፈርዳ ፣ ከቤኔሻንጉል ፣ ከኦሞ ወንዝ ዙሪያ ወዘተርፈ የተፈናቀሉትን ኢትዮጵያውያን በመሰደድ ላይ እያሉ የሞቱባቸውን እናቶቻቸውን ፣ አባቶቻቸውን ፣ ልጆቻቸውን ወዘተርፈ ተቀምጠውም ሆነ ቆመው ማልቀሻና መቅበርያ ቦታ አልነበራቸውም፤ ያጡት አገር ነበርና ።

ወደ ሰማይ እንዳይበሩ ክንፍ የላቸው
ወደ መሬት እንዳይገቡ ራዳግራም የላቸው
ወገን በሙሉ ከጅብ የማያስጥል አህያ ሆነባቸው
መሬት አጥተው በገዛ አገራቸው
ምን ይሁኑ ምን ይዋጣቸው ?

እናትም ብትሞት ባገር ይለቀሳል
አባት የሞተ እንደሆን ባገር ይለቀሳል
ዘመድ አዝማድ ሲሞት ባገር ይለቀሳል

ሃገር የሞት እንደሆን ወዴት ይደረሳል? የተሰኘው የአበው ብሂል የዚህ ጽሑፍ ተልዕኮ በሚገባ የሚገልጸው ይመስለኛል ።

ከታጠቅ መንጂ
11/12/2014